## የኮሮና ቫይረስ በሽታ (የኮቪድ-19) አስመልክቶ የተዘጋጀ መግለጫ

የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኮሮና ቫይረስ በሽታ ቅኝትን ከማጠናከር አኳያ በተለያዩ ሆስፒታሎች በተኝቶ ማከሚያ ውስጥ ያሉ የከፍተኛ አጣዳፊ የመተንፈሻ አካል በሽታ (Severe Acute Respiratory Illness) ካለባቸው ሰዎች ላይ ናሙና በመውሰድ የኮሮና ቫይረስ ምርመራ እያደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ ከቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ከተወሰደ ናሙና ውስጥ አንዲት ታካሚ ላይ የኮሮና ቫይረስ እንደተገኘባት በመጀመሪያ የላብራቶሪ ምርመራ በመታወቁ ለህብረተሰቡ መጋቢት 18፣ 2012 ዓ.ም በተሰጠው መግለጫ ማሳወቃችን ይታወቃል፡፡ ይህች 16ኛ ታማሚ የ24 ዓመት ኢትዮጵያዊት ስትሆን የውጭ ሀገር የጉዞ ታሪክ የሌላት እንዲሁም በበሽታው መያዙ ከተረጋገጡ ሰዎች ጋር ንክኪ ያልነበራት በመሆኑ በድጋሚ ሶስት ጊዜ በተደረገላት የላብራቶሪ ምርመራ ሶስቱም ውጤት ኔጌቲቭ በመሆኑ በቫይረሱ አለመያዝዋን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይሁንና ታማሚዋ የቆየ ተጓዳኝ የጤና ችግር ያለባት በመሆኑ የህክምና ክትትል እየተደረገላት ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የህክምና ክትትል ሲያደርጉላት የነበሩ የሆስፒታሉ ሰራተኞችና ሌሎች ከነሱ ጋር ግንኙነት የነበራቸው በድምሩ 24 ሰራተኞች ለጥንቃቄ ሲባል በተዘጋጀው ለይቶ ማቆያ ውስጥ ክትትል እየተደረገላቸው እንዲቆዩ የተደረገ ሲሆን በሚቀጥሉት ቀናት ወደ ስራ ገበታቸውና ቤተሰቦቻቸው የሚመለሱ ይሆናል።

ለተጨማሪ መረጃ በነፃ የስልክ መስመር 8335 ወይም 952 ፤ በመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796 ወይም በኢሜል አድራሻችን ephieoc@gmail.com በመጠቀም ማግኘት ይቻላል፡፡

ዶ/ር ሊያ ታደሰ
የጤና ሚኒስቴር
መጋቢት 21፣ 2012 ዓ.ም